ቀን፡- ህዳር 04 ቀን 2013 ዓ.ም.

# ማስታወቂያ

በስዊዘርላንድ እና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸው አገራት ለምትገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት በሙሉ፣

ጉዳዩ፡- የሰብዓዊ ድጋፍ አሰባሰብን ስለማስተባበር፣

መንግስት ከህወሀት ጋር ያለውን ችግር በሰላማዊ መንገድ በውይይት ለመፍታት ተከታታይ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። ህወሀት ይህንን ሰላማዊ አካሄድ ባለመቀበልና ለሚያከናውናቸው ህገወጥ ተግባራት መንግስት ያሳየውን ትዕግስት ከድክመት በመቁጠርና በአፍርሽ ተግባሩ በመቀጠል ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም. ከምሽቱ አራት ሰዓት ጀምሮ ከ20 ዓመት በላይ በትግራይ ክልል የህገሩንና የህዝቡን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ በኖረው የሰሜን ዕዝ የመከላከያ ሰራዊት ላይ ባልተጠበቀ ሁኔታ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ፈጽሟል። ከዚህም ባሻገር በዳንሻ አካባቢ ባለው የመከላከያ ሰራዊት ላይ ያልተጠበቀ ድንገተኛ ጥቃት በመፈጸም የመጨረሻውን ቀይ መስመር በማለፉ መንግስት የአገሩንና የህዝቡን ደህንነት እንዲሁም የመከላከያ ሰራዊቱን ክብር ለማስጠበቅ በህገ መንግስቱ የተጣለበትን አገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት እንዲገደድ አድርጎታል።

ከዚህ አንፃር በአገር ሉዓላዊነትና በህዝቡ ላይ የተፈፀመውን ክህደትና የጭካኔ ተግባር ለመቀልበስና ህግና ስርዓትን ለማስከበር በግንባሩ ተሰልፎ ከፍተኛ ተጋድሎ እየፈፀመ የሚገኘውን ጀግናውን የመከላከያ ሰራዊታችንን በሞራል፣ በገንዘብና በቁሳቁስ ለመደገፍ በሀገር ውስጥ ህዝቡ በከፍተኛ ሁኔታ እየተረባረበ ይገኛል። በተመሳሳይ ሁኔታ በውጭ ሀገር በተለይም በስዊዘርላንድ እና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸው አገራት የሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት አገሩንና ህዝቡን በደሙና በአጥንቱ እየዋጀ የሚገኘውን ጀግናውን የመከላከያ ሰራዊታችንን የሚደግፉበት ሁኔታ እንዲመቻችላቸው እየጠየቁ ይገኛሉ።

በዚሁ መሰረት በስዊዘርላንድና ሚሲዮኑ በሚሸፍናቸው አገራት የምትገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ባቀረባችሁት ጥያቄ መሰረት ለመከላከያ ሰራዊታችን የምታደርጉትን ድጋፍ ከዚህ በሚከተለው የባንክ አካውንት ገቢ በማድረግ ደረሰኙን በgeneve.embassy@mfa.gov.et እንድትልኩ በአክብሮት እንጠይቃለን።

Mission Permanent d'Ethiopie,

Bank: - UBS

IBAN: - CH4900279279 HU21 6536 0

በጄኔቭ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት

Permanent Mission of the Federal Democratic Republic of Ethiopia to the UN, Geneva